# በሰይጣን የሚወደዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

## ክፍል ፩

ከተስፋዬ ሮበሌ

ከአገረ አሜሪካ

ሰይጣን ዐላማውን ከዳር ለማድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይጠቅሳል:: ስለዚህ ቍም ነገሩ “ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተጠቅሶአል” የሚለው ሳይሆን፣ “የተጠቀሰው ምንባብ በርግጥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት በትክክል የተከተለ ነውን?” የሚለው ጕዳይ ነው:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አርባ ቀን ጾሞ ከጸለየ በኋላ ሰይጣን ብርቱ ፈተና የፈተነው፣ ብሉያትን እየጠቀሰና እያጣቀሰ ነው (ሉቃስ 4÷3-13 እንዲሁም ከምስስለ ወንጌላት ተጓዳኝ ምንባባቱን ይመልከቱ)::

ገረጅም ዓመት በፊት አንድ እናት፣ “እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የዋህ የለም፤ ሁሉም ማለት ለሚፈልገው ነገር የሚስማማ ነገር ያገኝበታል” ይሉ ነበር:: ለዘብተኛ አቋም ያላቸው የነገረ መለኮት ምሁራን፣ “መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ ሊታረቁ የማይችሉ አስተምህሮችን በአንድ ጊዜ ያጸድቃል” በማለት የኚህን እናት አሳብ በሌላ መልክ ያቀርቡታል::

መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ የሚጣረስ አንዳችም ትምህርት የለውም:: እንዲያውም ለአፌዎተ ቃልነቱ (የእስትንፋሰ መለኮትነቱ) አንዱ ማስረጃ በተለያየ ዘመን፣ በተለያየ ጸሓፊ፣ በተለያየ የኑሮ ደረጃ፣ በተለያየ የትምህርት ዕርከን ወዘተ ባሉ ሰዎች ተጽፎ ነገር ግን አንድ ወጥ አስተምህሮ ይዞ መገኘቱ ነው:: ይህ ሲባል ግን ስልቹ አንባቢ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል አንብቦ ትምህርቱን ሁሉ ገንዘቡ ማድረግ ይችላል ማለት አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል አንብቦ ለመረዳት፣ እጅግ ብዙ ጥንቃቄና እጅግ ብርቱ ጥረት ይፈልጋል:: የተጻፈበት ቋንቋ፣ ዘመን፣ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ባህል፣ ሥልጣኔ ወዘተ ከእኛ ከዘመነኞቹ እጅግ መራቁ በተወሰነም መጠን ቢሆን፣ ፍለጋችንን አድካሚ አድርጎታል::

እኔ ዛሬ “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” ወይም “ኦንሊ ጂሰስ” በመባል የሚታወቀው የሃይማኖት ድርጅት “አብና ወልድ አንድ አካላት ናቸው”፣ ወይም “ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው” ለሚለው ትምህርቱ ማጠናከሪያ ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ አዘውትሮ የሚጠቅሳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በቅርበት እመረምራለሁ:: ይህ ደግሞ በተሳሳተ እምነት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለማምጣት ብቻ ሳይሆን ራሳንም ከመናፍቃን እንቅስቃሴ ለመጠበቅ እንዲሁም መሠረተ እምነታችንን በትክክል ለመረዳት ትልቅ እርዳታ አለው:: እንግዲያው ወደ ምርመራችን እንቅለቅ:—

## ኢሳይያስ 9÷6

**"ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም፣ ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል"**

כִּֽי־יֶ֣לֶד יֻלַּד־לָ֗נוּ בֵּ֚ן נִתַּן־לָ֔נוּ וַתְּהִ֥י הַמִּשְׂרָ֖ה עַל־שִׁכְמ֑וֹ וַיִּקְרָ֨א שְׁמ֜וֹ פֶּ֠לֶא יוֹעֵץ֙ אֵ֣ל גִּבּ֔וֹר אֲבִיעַ֖ד שַׂר־שָׁלֽוֹם׃[1]

በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱት ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ እንዲሁም የሃይማኖት ድርጅቱ የውጭ ጸሓፍት፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው (አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው) ለሚለው አስተምህሮአቸው ማስደገፊያ፣ አዘውትረው የሚጠቅሱት ተወዳጅ ክፍል ነው (ኢሳይያስ 9÷6)[2]። ይህን ክፍል አስመልክቶ ድርጅቱ በተለያየ ጊዜ ያወጣቸውን ትምህርቶች በእማኝነት እናቅርብ:—

> "በኢሳይያስ 9÷6 ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኀያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል' የተባለለት ያ አንዱ ኀያል አምላክና የዘላለም አባት፣ በሥጋ መምጣቱን ያስረዳል። ይህ ሕፃን ሆኖ የተገለጠው አብም ወልድም ነው። ሙሉ አካልና ሙሉ ሰውም ነው...አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው"[3]።
>
> "ኢሳ. 9÷6 ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተነበየው ሕፃኑ ወልድም አብም ኀያል አምላክም በመሆኑ ምክንያት ከገዛ ራሱ ጋር ሊያስታርቀን ሙሉ ሥልጣን አለው"[4]።
>
> "ኢሳይያስ 9÷6 ሁለት መለኮት፣ ሁለት መንፈስ የለምና መንፈስና ሥጋ አብና ወልድ በውሕደት አንድ አካል ስለሆኑ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ በመለኮትነቱ የሰማይና የምድር ፈጣሪ እግዚአብሔር አብ ነው ብለን እናምናለን...አባቱ በውስጡ በውሕደት ካለ፣ ለምን ወደ ሰማይ እየተመለከተ ወደ አባቱ ጸለየ? የሚሉን መልሱ በኢሳ 53፣ በ2ቆሮ 5÷18-21፣ በኤር 31÷31-34፣ በኤፌ 2÷1-20 የተጻፈውን ሲመለከቱ፣ ክርስቶስ በእኛ ፈንታ እንጂ ለራሱ ነጻነት እንዳልተጨነቀ፣ የማስታረቅ ሥራን ብቻ እንደ ሠራ ያመለክቱናልና የእርሱን የምልጃ ሥራ ከንቱ ባናደርግ መልካም ነው እንላለን"[5]።

የመሥራቹ ግለሰብ ጽሑፍ እንዲሁም የድርጅቱ አንቀጸ ሃይማኖት እንደሚገልጸው፣ በርግጥ ይህ ምንባብ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "አብም ወልድም ነው"፣ "አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው"፣ "መንፈስና ሥጋ፣ አብና ወልድ በውሕደት አንድ" አካል ሆነዋል ይላልን? በውኑ ኢየሱስ ክርስቶስና አብ አንድ ስብእና (Person) አላቸውን?

---

[1] *Biblia Hebraica Stuttgartensia: With Werkgroep Informatica, Vrije Universiteit Morphology; Bible. O.T. Hebrew. Werkgroep Informatica, Vrije Universiteit.*, Is 9:5 (Logos Bible Software, 2006).

[2] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* (አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1978), ገጽ 40-41። *የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች* አንቀጽ 2፤ ገጽ 4። David K. Bernard, *The Oneness of God* (Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1983), 66.

[3] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* 40።

[4] ዝኒ ከማሁ፤ 108።

[5] *የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች* አንቀጽ 2፤ ገጽ 4።

ድርጅቱ ይህን ክፍል መደገፊያ በማድረግ ወደዚህ ድምዳሜ እንዴት እንደ ደረሰ የሚገልጸው በሚከተለው መልኩ ነው:— በዚህ ምንባብ "አባት" የሚለው የአማርኛ ቃል፣ በግእዝ "አብ" የሚል አቻ ትርጓሜ አለው:: ስለዚህ ኢየሱስ "አባት" ነው ማለት ኢየሱስ "አብ" ነው ማለት ነው::

ይህ ምንባብ የድርጅቱን መሠረተ እምነት የሚደግፍ አንዳችም ትምህርት የለውም:: እንዲያውም ክፍሉን በዚህ መልክ ማብራራት ግለሰቦቹ ለቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ለነገረ መለኮት እጅግ ባይተዋር መሆናቸውን፣ ድርጅቱም ያረጀ ያፈጀ ኑፋቄ በመከተል ላይ እንደሚገኝ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው:: እስቲ ክፍሉን በሰከነ ልብ በቅርበት ወደ መመርመሩ እንቅለቅ[6]:—

አንደኛ፤ "በብሉይ ኪዳንም ሆነ በዕብራውያንና በዐረቡ ባህል፣ "አባት" (በዕብራይስጡ፣ "አብ" "אָב") በተጸውዖ (በመጠሪያ) ስምነት ካገለገለ፣ የስሙ ባለቤት (በዚህ ቃል የሚጠራው ግለሰብ) ከሚጠራበት ስም ጋር አንድ ዐይነት ባሕርይ አለው ማለት ነው"[7]:: ጥቂት አስረጆችን እንመልከት:— "አቢዓልቦን" (אֲבִי־עַלְבוֹן) (2ሳሙኤል 23÷31) የሚለው ጣምራ ስም "አቢ" "אָב" ማለትም "አባት" እንዲሁም "ዓልቦን" "עַלְבוֹן" ማለት "ጠንካራ" ከሚሉት ቃላት የተዋቀረ ነው:: በተገናኝ ሲነበብ (አጫፍረን ስናነበው)፣ የጥንካሬ አባት ወይም እጅግ በጣም ጠንካራ የሚል ትርጉም ይወክላል:: "አቢያሳፍ" "אֲבִיאָסָף" (ዘፀአት 6÷24)[8] ማለት፣ "አቢ" "אָב" "አባት" እንዲሁም "አሳፍ" "אָסָף" ማለት "ሰብሳቢ" አጫፍረን ስናነበው በሰብሳቢነት ትልቅ ስም የተጐናጸፈ ማለት ነው:: "አቢጋኤል" "אֲבִיגַיִל" (1ዜና 2÷16) ማለት፣ "አቢ" "אָב" "አባት" እንዲሁም "ጋኤል" "" ማለት "ማለት ጠንካራ" በተገናኝ ስናነበው ከፍ የማለት አባት ወይም እጅግ በጣም ከፍ ይልሽ ማለት ነው:: አቢጋኤል የሚለው ስም የሴት መጠሪያ መሆኑን ልብ ይሏል:: አባት ነሽ ማለት ሳይሆን፣ ከፍ ያልሽ ነሽ ማለት ብቻ ነው (በአማርኛ "ላቀች" እንደሚለው ስም ማለት ነው)::

በአጭሩ "አብ" ወይም አባት (በዕብራይስጡ፣ "אָב") የሚለው ቃል አባትነትን የሚያሳይ ሳይሆን፣ ከፊለፊቱ ያለውን ስም የሚያደምቅ ቅጽል ነው፤ ይኸውም "የጥንካሬ አባት"—በጣም ጠንካራ፣ "የመሰብሰብ አባት"—እጅግ በጣም ታላቅ ሰብሳቢ፣ "ከፍ የማለት አባት"—እጅግ በጣም ከፍ ያለች ወዘተ[9]::

---

[6] ይህ ትንታኔ በአብዛኛው የተወሰደው፣ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ዐበይት መናፍቃን* (አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፤ 1993), ገጽ 144-145 ላይ ነው::

[7] Albert Barnes, *Notes on the Old Testament Explanatory and Practical Isaiah.* Vol. I (Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1950 reprint), 193.

[8] በብሉይ ኪዳን ሁለት የተለያዩ ሰዎች በዚህ ስም ተጠርተዋል፤ ይኸውም የቀድሞ የናባል ሚስት:— 1ሳሙ 25÷3–42፤ 27:3፤ 30÷5፤ 2ሳሙ. 2÷2፤ 3÷3፤ 1ዜና 3÷1፤ እንዲሁም የንጉሥ ዳዊት እኅት 2ሳሙ. 17÷25፤ 1ዜና 2÷16:17+:: James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).

[9] እኛ በናሙናነት የተወሰኑትን አቀረብን እንጂ፣ ብሉይ ኪዳን በዚህ መልክ የተዋቀሩ እጅግ በርካታ ስሞች አሉ:: እነዚህ ስሞች ደግሞ የወንድ መጠሪያ ብቻ ሳይሆኑ የሴት እንዲያውም አንዳንዴ ግዑዝ ነገሮችንም ለማመልከት ጥቅም ላይ ውለዋል:: ሙሉ መረጃው እነሆ:— በዚህ ቦታ የተከተልነው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን ሳይሆን፣ የዕብራይስጡን ንበት ነው:: አቢኤል—אֲבִיאֵל (1ሳሙ. 9÷1፤ 14÷51+፤ 1ዜና 11÷32+)፤ አቢአሳፍ—אֲבִיאָסָף (ዘፀ. 6÷24+)፤ አቢብ—אָבִיב (ዘፀ. 9÷31፤ ዘሌ. 2÷14+)፤ አቢባል—אֲבִיבַעַל (2ሳሙ 23÷31+)፤ አቢዳን—אֲבִידָן (ዘኍ. 1÷11፤ 2÷22፤ 7÷60:65፤ 10÷24+)፤ አቢዳ—אֲבִידָע (ዘፍ. 25÷4፤ 1ዜና 1÷33+)፤ አቢያህ—אֲבִיָּה (1ዜና 7÷8፤ 1ሳሙ. 8÷2፤ 1ነገ. 14÷1፤ 1ዜና 24÷10፤ 1ዜና 3÷10፤ 2 2÷2፤ 1ዜና 29÷1)፤ አቢያሁ—אֲבִיָּהוּ (2ዜና 13÷20-21+)፤ አቢሁ—אֲבִיהוּא (ዘፀ. 6÷23፤ ዘሌ. 10÷1፤ ዘኍ 3÷2፤ 1ዜና 5÷29)፤ አቢሁድ—אֲבִיהוּד

በዚህ ክፍል “አባት” (“אָב”) የሚለው ቃል አባትነትን አመላካች ነው ከተባለ፣ “ጥንካሬ የሚባልን ሰው የወለደ ወላጅ”፣ “መሰብሰብን የወለደ አባት” ወዘተረፈ ትርጓሜ ሊይዝ ነው ማለት ነው:: ይህ መቼም የቋንቋ ባለቤት ለሆነ የሰው ዘር በሙሉ እንግዳ አካሄድ ነው:: አንዳችም ትርጉም ሊወክልም በጭራሽ አይችልም፤ ምክንያቱም መሰብሰብ፣ ጥንካሬ፣ ከፍ ማለት ወዘተ የሚሉት ስያሜዎች የሚወለዱ ልጆች፣ ወላጅ አባትም የሚኖራቸው ነገሮች አይደሉምና:: ይህ ዐይነቱ ፍቺ ስሑት መሆኑ የሚያግባባን ከሆነ፣ “አብ” የሚለው ቃል ማድመቂያ ቅጽል እንጂ፣ አባትነትን ሊያሳይ በጭራሽ አይችልም::

በኢሳይያስ 9÷6 ላይ፣ “የዘላለም አባት” ተብሎ የተተረጐምው ቃል በዕብራይስጥ “አቢአድ” “אֲבִיעַד” ከሁለት ስሞች የተጫፈረ ስያሜ ነው:: ይኸውም “አብ” እና “አድ” ሚለው ሲሆን፣ ትርጉማቸውም “አባት” እና “ዘላለም” ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከላይ እንዳየናቸው “በአባት” እንደ ተጫፈሩ ስያሜዎች፣ የክርስቶስን ዘላለማዊነት የሚያሳይ እንጂ (ዕብራውያን 1÷2፤ 11÷3፤ ራእይ 1÷7-8፤ 1÷17-18፤ 2÷8፤ 22÷13)፣ “ኢየሱስ አብ ነው” ወይም “አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው” ወይም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ፣ “የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት” (2ቆሮንቶስ 1÷3) ነው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም[10]::

ሁለተኛ፤ “አባት” (በዕብራይስጡ፣ “አብ” ወይም “አቭ” “אָב”) የሚለው ቃል ዘላለማዊነቱን የሚያጸምቅ/የሚቀጽል ሳይሆን፣ ኢየሱስ አባት መሆኑን የሚያመለክት ነው ቢባል እንኳ (እንደዚያ እንዳልሆነ ከላይ በግልጽ ለመሞገት ሞክረናል)፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው ማለት አይደለም:: እኔ አባት ነኝ፤ ነገር ግን የራሴ አባት አይደለሁም:: ኢየሱስ “አባት” ቢሆን እንኳ፣ ከፍጡራን ጋር ያለውን ግንኙነት አመላካች እንጂ፣ ኢየሱስ ራሱ “አባቴ” የሚለው አብ እርሱ ራሱን ነው ማለት አይደለም[11]

(1ዜና 8÷3+)፤ አቢኀይል—אֲבִיהַיִל (1ዜና 2÷29+፤ 2ዜና 11÷18+)፤ አቢዮን—אֶבְיוֹן (ዘፀ. 23÷6)፤ አቢኦና—אֲבִיוֹנָה (ምክ. 12÷5+)፤ አቢቱብ—אֲבִיטוּב (ዜና 8÷11+)፤ አቢታል—אֲבִיטָל (2ሳሙ. 3÷4፤ 1ዜና 3÷3+)፤ አቢያም—אֲבִיָּם (1ነገ. 14÷31፤ 15÷1:7:8+)፤ አቢማኤል—אֲבִימָאֵל (ዘፍ. 10÷28፤ 1ዜና 1÷22+)፤ አቢሜሌክ—אֲבִימֶלֶךְ (ዘፍ. 20÷2፤ መሳ. 9÷1፤ 1ዜና 18÷16፤ መዝ. 31÷1 ርእስ)፤ አቢናዳብ—אֲבִינָדָב (1ሳሙ. 7÷1፤ 2ሳሙ. 6÷3:4፤ 1ዜና 13÷7+፤ 1ሳሙ. 16÷8 ፤ 17÷13፤ 1ዜና 2÷13+፤ 1ሳሙ. 31÷2 1ዜና 8÷33፤ 9÷39፤ 10÷2+)፤ አቢኖአም—אֲבִינֹעַם (መሳ. 4÷6:12፤ 5÷1: 12+)፤ አቢነር—אֲבִינֵר (መሳ. 14÷50+)፤ አቢኤዘር—אֲבִיעֶזֶר (ኢያ. 17÷2፤ መሳ. 6÷34፤ 8÷2+፤ 6÷11:24፤ 8÷32፤ 2ሳሙ. 23÷27፤ 1ዜና 11÷28፤ 27÷12+፤: 1ዜና 7÷18+)፤ አቢኢዝሪ—אֲבִי עֶזְרִי (መሳ. 6÷11:24፤ 8÷32+)፤ አቢር—אָבִיר (ዘፍ. 49÷24፤ መዝ. 132÷2:5፤ ኢሳ. 1÷24፤ 49÷26፤ 60÷16+)፤ አቢራም—אֲבִירָם (ዘኍ. 16÷1-7፤ 26÷9፤ ዘዳ. 11÷6፤ መዝ. 106÷17+፤ 1ነገ. 16÷34+)፤ አቢሳግ—אֲבִישַׁג (1ነገ. 1÷3:15፤ 2÷17:21:22+)፤ አቢሱአ—אֲבִישׁוּעַ (1ዜና 8÷4+፤ 5÷30፤ ዕዝ. 7÷5+)፤ አቢሱር—אֲבִישׁוּר (1ዜና 2÷28:29+)፤ አቢሳይ—אֲבִישַׁי (1ሳሙ. 26÷6፤ 2ሳሙ. 2÷18)፤ አቢሰሎም—אֲבִישָׁלוֹם (1ነገ. 15÷2:10+)፤ አቢያታር—אֲבִישָׁלוֹם (1ሳሙ. 22÷20)—James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).

[10] ምናልባት አንዳንድ ሰዎች “አቢአድ” (“אֲבִיעַד”) የሚለው ቃል እንደሌሎች የተጸውዖ (የመጠሪያ ስሞች) “አቢአድ” ለምን አልተባለም፤ ለምን “ኀያል አምላክ” ተብሎ መተርጐም አስፈለገው? የሚል ጥያቄ ሊያነሡ ይችላሉ:: “አቢ” ወይም “አብ” በሚሉ ስሞች የተጫፈሩት የተጸውዖ ስሞች ናቸው፤ ይህ ግን ለአምላክ መጠሪያነት በማዕረግ ስምነት ጥቅም ላይ የዋለ ነው፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተተርጕሞ መቅረቡ አስፈላጊ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው:: በተመሳሳይ መንገድ ከዚህ ስም ጋር ተመሳሳይ ትርጓሜ ያለውንና ለአብ መጠሪያነት ጥቅም ላይ የዋለውን የማዕረግ ስም ከሚከተሉት ምንባባት ይመለከቷል:— አቢር—אָבִיר (ዘፍ. 49÷24፤ መዝ. 132÷2:5፤ ኢሳ. 1÷24፤ 49÷26፤ 60÷16+)::

[11] Beisner, 32.

(አባት፣ ልጅ፣ እናት፣ ወንድም፣ እኅት ወዘተ የሚሉት ቃላት ግንኙነትን አመላካች ቃላት መሆናቸው በጭራሽ ሊጠፉን አይገባም)።

ሦስተኛ፤ የድርጅቱ መምህራን ከላይ ባየናቸው የማይነቀሱ የማይገሠሡ ማስረጃዎች በእማኝነት እያቀረብን ስንሞግታቸው፣ የሚከተለውን የሙግት አካሄድ በመከተል ዐቢይ ሙግቱን እንደ ዋዛ አድበስብሰው ማለፍ ይፈልጋሉ። ይኸውም:— ክፍሉ ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው ባይል እንኳ፣ ኢየሱስ አባት እንደ ሆነ ሊገልጽ ይችላል[12]። ኢየሱስ አብ ወይም አባት ከተባለ ደግሞ የሚከተለው ሙግት ስሙር ሙግት በመሆን መሠረተ እምነታችን ትክክለኛ ይሆናል:— (1) አንድ እግዚአብሔር ብቻ ካለ፣ (2) ይህም እግዚአብሔር አባት ከሆነ፣ (3) ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ኢየሱስ አባት ነው ማለት ነው።

ይህ ፍጹም ስሑት ሙግት ነው። ምክንያቱም በእነዚህ የሙግት ነጥቦች ውስጥ “አባት” እና “አምላክ” የሚሉት ቃላት አምላካዊ ባሕርይን (nature or essence) እንጂ፣ አካላዊ ሕልውናን (person) አመላካች አይደሉም። በአንድ ሙግት ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት የተለያየ ትርጓሜ የሚወክሉ ከሆነ “የአሻሚ ትርጓሜ ተፋልሶ” (“በእንግሊዝኛው Fallacy of equivocation”) ስለሚከሠት ሙግቱ ስሑት ሙግት በመሆን ይጠናቀቃል። “የአሻሚ ትርጓሜ ተፋልሶ” በግልጽ ሊያሳዩ የሚችሉ ሁለት ናሙናዎችን እንመልከት:— (1) ከእንስሳት ኋላ ያለው አካል ጭራ ይባላል። (2) ከአውሮፕላን ኋላ ያለው አካል የአውሮፕላኑ ጭራ ነው። (3) ስለዚህ ከአውሮፕላን ኋላ ያለው አካል የእንስሳ አካል ነው። በዚህ ሙግት ውስጥ “ጭራ” የሚለው ቃል፣ ሁለት የተለያየ ትርጒም ወክሎ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ሌላ አስረጅ እንጨምር:— (1) ቀበሮ ሁሉ ሥጋ በል እንስሳ ነው። (2) ኢየሱስ ንጉሥ ሄሮድስን ቀበሮ ብሎታል (ሉቃስ 13÷32)። (3) ስለዚህ ንጉሥ ሄሮድስ ሥጋ በል ሰው ነበር። በዚህም ሙግት ውስጥ “ቀበሮ” የሚለው ቃል ሁለት የተለያየ ትርጒም ወክሎ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ስለዚህ የእነዚህ ሙግቶች ድምዳሜ ስሕተት ሊሆኑ ችለዋል።

ከላይ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ስሕተት በአስረጅነት ካመጣናቸው ሙግቶች የተሻለ አይደለም፤ በእነዚህ ሙግቶች የሚታየው ተመሳሳይ ችግር ነው፣ በዚህም ሙግቶች ውስጥ የሚስተዋለው። ይኸውም ስለባሕርይ (nature or essence) የሚናገሩትን ማስረጃዎች ከአካል (person) ጋር አቀላቅሎ  አቅርቧልና። ይህ ዐይነቱ አካሄድ ደግሞ፣ የርቱዕ ሙግት አካሄድ አይደለም።

አራተኛ፤ ልብ ልናደርገው የሚገባን ሌላው ነጥብ፣ ይህ ሙግት ባሕርይንና አካልን ክፉኛ ማጣናበሩ (ማምታታቱ) ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አብ ብቻ አባት ነው፤ ልጁ አባት ከተባለ ደግሞ እርሱ ራሱ ዞሮ መምጣቱን የሚያሳይ ነው የሚለውን ስሑት መቅድመ ልባዌ ታሳቢ ያደረገ ሙግት ነው[13]። ከላይ ለመጠቆም እንደ ሞከርነው፣ “አባት” የሚለው ቃል ግንኙነትን አመላካች ከመሆኑም ባሻገር፣ አብ አባት እንደ ሆነው ሁሉ ወልድ አባት መሆን የሚከለክለው አንዳችም ምክንያት የለም።

---

[12] በፍጹም ሊገልጽ አይችልም፤ ክፍሉ ኢየሱስ አባት እንደ ሆነ የሚናገር አይደለም። ነገር ግን ኢየሱስ ከምናስበውና ከምንገምተው በላይ ጊዜ–የለሽ (ዘላለማዊ) እንደ ሆነ የሚገልጽ እንጂ።

[13] ድርጅቱ ትምህርተ ሥላሴን ለመተቸት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሙግት አካሄድ ይከተላል። ይህ የሙግት አካሄድ ፍጹም ስሕተት ነው። ትምህርተ ሥላሴን አስመልክቶ የሚቀርቡትን ተመሳሳይ የሙግት አካሄዶች ስሕተታቸውን ለመረዳት የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ *የትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ምክንዮአዊ ትንታኔ* የሚለውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

አምስተኛ፣ ኢሳይያስ 9÷6 ኢየሱስ ራሱ አብ መሆኑን ወይም አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን የሚያስተምር ክፍል ነው ብሎ የጻፈ አንዳችም የብሉይ ኪዳን ሊቅ የለም። እልቀ- መሳፍርት የሌላቸው የትንቢተ ኢሳይያስ ትርጓሜ መጻሕፍት በእጃችን አሉ። እነዚህም መጻሕፍት በአይሁድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት፣ በካቶሊክ ምሁራን፣ በኦርቶዶክስ መምህራን እንዲሁም ለዘብተኛ አቋም ባላቸው የነገረ መለኮት ትምህርተ ዘለቅ የተጻፉ ናቸው። ነገር ግን ያለድርጅቱ መምህራን በስተቀር፣ ይህን ክፍል በዚህ መልክ የተረጐመው አንዳችም ተኣማኒ ባለሥልጣን የለም። በአጠቃላይ ኢሳይያስ 9÷6ን በመጥቀስ፣ ኢየሱስ "አብም ወልድም ነው" ወይም "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው" ማለት ስሕተት ነው።

## ዮሐንስ 10÷30
## "እኔና አብ አንድ ነን"
"ἐγὼ καὶ ὁ πατὴρ ἕν ἐσμεν"

ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው (አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው) ለሚለው "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ ማስደገፊያ ተብሎ ከሚቀርቡ የድርጅቱ ተወዳጅ ክፍሎች መኻል አንዱ፣ ዮሐንስ 10÷30 ነው[14]። የድርጅቱ መሥራችና ዕውቅ መምህር ቄስ ተክለ ማርያም ይህን ክፍል ተመለከተ እንዲህ ይላሉ፡—

> "ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 10÷30 እኔና አብ አንድ ነን ብሎ በማወጁ፣ አብ ወልድ ውስጥ በውሕደት መኖሩን መግለጡ እንደ ሆነ እንረዳለን"[15]።
>
> "እግዚአብሔር አብ የላከልን ልጅ ሰማያዊ ስለሆነ የባሕርይው ልጁ ነውና በአካል ከአብ የተለየ አይደለም። ወልድ የአብ መልክ ነው። እኔና አብ አንድ ነን ብሎ በድፍረት መናገር የሚችለው አብና ወልድ በውሕደት በአንድ አካል ውስጥ ስላሉ ብቻ ነው ዮሐ. 10÷30"[16]።

አስገራሚው ንጽጽር በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ኑፋቄ ለዓለም ያስተዋወቀው ሰባልዮስ[17]፣ ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው ለማለት አዘወትሮ ይጠቅሳቸው ከነበሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት ውስጥ ይህ አንዱ እንደ ነበር፣ በርካታ የታሪክ ድርሳናት ይገልጻሉ። ዛሬም የሰባልዮስ መንፈሳውያን ልጆች ይህንኑ ዘመን ያፈጀ ኑፋቄ ከትቢያ ለማንሣት፣ ይህንኑ ጥቅስ ደግሞው ደጋግመው ይጠቅሳሉ። ክፍሉ ተደጋግሞ መጠቀሱ ቀዳማይ አስተምህሮው እንዲወይብ (እንዲደበዝዝ) ወይም በፊት ከሚያስተምረው ትምህርት ተቃራኒውን ትርጒም እንዲይዝ አያደርገውም። ቤተ ክርስቲያን በዚያን ዘመን ይህን ኑፋቄ፣ "ውጉዝ ከመሰባልዮስ" እንዳለችው ሁሉ፣ ዛሬም በጽናት አራጥቃነቱን (ኑፋቄነቱን) ታጸናለች። ይህን የምታደርገው ግን እንዲያው እውር ድንብሩን በወጣ ጭፍን ጥላቻ ሳይሆን፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን እማኝነት በጥልቀት በመረመረ መንገድ ነው። "እኔና አብ አንድ ነን" (ዮሐንስ 10÷30) ማለቱ፣ አብ ወልድን ማደሪያው ማድረጉን ወይም አብና ወልድ በአካል አንድ መሆናቸውን የሚገልጽ አይደለም።

---

14 ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* 43 David K. Bernard, *The Oneness of God* 67

15 ዝኒ ከማሁ፣ 43።

16 ዝኒ ከማሁ፣ 68።

17

አንደኛ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ አብ ነኝ ለማለት ፈልጎ ቢሆን ኖሮ፣ “እኔ አብ ነኝ” ወይም “አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው” ማለት ነበረበት። ምክንያቱም ይህ መደበኛው ንግግር እንዲሁም በሰዋስው ትክክለኛ የሆነው።

ሁለተኛ፤ “እኔና አብ አንድ ነን”፣ “አንድ ነን” ተብሎ ወደ አማርኛ የተተረጐመው፣ “ሒን ሒስሜን” (“ἕν ἐσμεν”) የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ የብዙ ቊጥር የሚያመለክት አንደኛ መደብ ነው። ኢየሱስ አብ ቢሆን ኖሮ፣ “ኢስሜን” (“ἐσμεν”-“we are”) የሚለውን የግሪክ ቃል ሳይሆን፣ አንደኛ መደብ ነጠላ ቊጥር የሆነውን “ኢጎ” ወይም “ኢጎ ሂሚ” (“ἐγὼ εἰμί”-“I am”) የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀም ነበር።

ሦስተኛ፤ “እኔና አብ አንድ ነን” ሲል፣ “አንድ” የሚለው ቃል ግሪኩ “ሂን” (“ἕν”) ሲሆን፣ ይህም የግዑዝ ጾታን የሚያመለክት ነው። የአብንና የወልድን የአካል አንድነት ለማመልከት ቢፈለግ ኖሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለኢየሱስ ክርስቶስ ተባዕታይ (የወንዴ) ጾታ እንደሚጠቀም ሁሉ፣ በዚህም ቦታ የተባዕታይ ጾታ የሚያመለክተውን የግሪክ ቃል (“ሔይስ” “εἷς”) ይጠቀም ነበር (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል—ማርቆስ 12÷29፤ 1ጢሞቴዎስ 2÷5)። ስመ ጥሩ የግሪክ ቋንቋ ሊቅ ኤ.ቲ. ሮበርትሰን ዮሐንስ 10÷30 በተመለከተ፣ “አንድ (“ሂን” “ἕν”) የሚለው ቃል የተባዕት ጾታን ሳይሆን የግዑዝ ጾታን የሚያመለክት መሆኑ፣ አካልን ሳይሆን አንድ ባሕርይን/ተፈጥሮን የሚያመለክት ነው”[18] ይላሉ። ስለዚህ በዚህ ቦታ “ሂን” (“ሂን” “ἕν”) የሚለው የግሪክ ቃል አንድ ዐይነት ባሕርይን እንጂ፣ አንድ አካልን የሚያመለክት አይደለም። ይኸውም አብና ወልድ አንድ ዐይነት ባሕርይ እንዳላቸው እንጂ፣ አብና ወልድ በአካል አንድ እንደ ሆኑ የሚያስተምር አይደለም።

አራተኛ፤ ኢየሱስ በዚሁ ክፍል አብን፣ “አባቴ” (ቊጥር 32) እንዲሁም “የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ” (ቊጥር 36) የሚሉትን ቃላት እየተናገረ፣ መልሶ ራሱን “አባት” ያደርጋል ማለት ስሕተት ነው።

አምስተኛ፤ በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ “አንድ” (ግሪኩ “ሂን” “ἕν”) የሚለውን ቃል የተጠቀመው የአካል አንድነትን ለማሳየት ነው ከተባለ፣ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ፣ “እኛም [አብና ወልድ] አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ” (ዮሐንስ 10÷30 ከ17÷21-23 ጋር ያነጻጽሩ) ሲል፣ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየላቸው ጸሎት፣ ደቀ መዛሙርቱ የዐላማ ወይም የልብ አንድነት ሳይሆን፣ በአካል አንድ እንዲሆኑ ነው ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ ፍጹም እንግዳ አስተሳሰብ ነው።

ስድስተኛ፤ ኢየሱስ፣ “እኔና አብ አንድ ነን” ሲል፣ “አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ” ያነሡበት ምክንያት (ቊጥር 31) ሕጋቸው፣ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተካከለ እግዚአብሔርን መሳደቡ ስለሆነ፣ በድንጋይ ይወገር ስለሚል ነው (ዘሌዋውያን 24÷16፤ ማቴዎስ 26÷66፤ ማርቆስ 14÷64፤ ዮሐንስ 19÷31፤ ሐዋርያት ሥራ 7÷58)[19]። በአጠቃላይ የክፍሉ ሰዋስውም ሆነ ዐውድ በግልጥ የሚያስተምረን

---

[18] በኮይኔ ግሪክ “አንድ” የሚለው ቅጽል ተባዕታይ (ሄይስ εἷς) አንስታይና (ሚያ μία) ግዑዝ ጾታን (ሒን ἕν) በሚያመለክት መልኩ የተደራጀ ነው። Archibald T. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Nashville Broadman Press, 1933), 5:186. እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: the New Testament Usage of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids: Baker, 1992), 258, n. 38 ይመለከቷል።

[19] በብሉይ ኪዳን በድንጋይ አስወግረው ከሚያስገድሉ ኀጢአቶች ወይም ወንጀሎች መኻል የሚከተሉት ይገኙበታል:— (1) ወላጅን መሳደብ (ዘፀ. 21÷15:17)፣ (2) እግዚአብሔርን መሳደብ (ዘሌ. 24÷14:16:23)፣ (3) ሰንበትን አለማክበር (ዘኍ. 15÷32-36፤ ዘፀ. 31÷14፤ 35÷2)፣ (4) ጥንቈላን ጨምሮ የሐሰትን ትንቢት ማናገር (ዘፀ. 22÷18፤ ዘሌ. 20÷27፤ ዘዳ. 13÷5፤ 18÷20)፣ (5) አመንዝራነት (ዘሌ. 20÷10፤ ዘዳ. 13÷5፤ 18÷20፤ 22÷21:23፤ ዘሌ. 21÷9)፣ (6) አስገድዶ መድፈር (ዘዳ. 22÷25)፣ (7) ሰዎችን

ጕዳይ፣ አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን ሳይሆን፣ አብና ወልድ አንድ ባሕርይ (essence) እንዳላቸው ነው:: ስለዚህ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መምህራን ይህን ክፍል በመጥቀስ ቃለ እግዚአብሔር አብና ወልድ አንድ መሆናቸውን ያስተምራሉ ማለታቸው ስሕተት ነው::

ለዛሬው እነዚህን ሁለት ምንባባት ከተመለከትን በሚቀጥለው ዕትም ተጨማሪ ክፍሎችን ይዤ ለመቅረብ እሞክራለሁ፤ አንድዬ ዕድሜና ጤናውን ይስጠን:: ቸር ሰንብቱልኝ:: ሡናይ ውእቱ::

---

አፍኖ መውሰድ (ዘፀ. 21÷16፤ ዘዳ. 24÷7)፣ (8) የአባትን ሚስት ማግባት ወይም እናትና ልጅን ማግባት (ዘሌ. 20÷11:14:15፤ ዘፀ. 22÷19)፣ (9) ጣዖትን ማምለክ (ዘሌ. 20÷2፤ ዘዳ. 13÷6:10:15፤ 17÷2-7)::